አላህና መልክተኛው አስካሪ መጠጥን፣ በክትን፣ አሳማንና ጣዖታትን ከመሸጥ ከልክለዋል።

ከጃቢር ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እርሱ የአላህ መልክተኛ
(የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መካ የተከፈተ ቀን መካ ውስጥ እንዲህ ሲሉ ሰማቸው: "አላህና መልክተኛው አስካሪ መጠጥን፣ በክትን፣ አሳማንና ጣዖታትን ከመሸጥ ከልክለዋል።" ለርሳቸውም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! የበክት ሞራን በርሱ ጀልባዎቻችን ይለቀለቃሉ፣ ቆዳችንን እንቀባበታለን፣ ሰዎች በርሱ መብራትን በመስራት ይጠቀማሉ። ንገሩን እርሱም ክልክል ነውን?" ተባሉ።
እርሳቸውም "በፍፁም እርሱም ክልክል ነው።" አሉና ቀጥለውም የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና)
በዚህ ጊዜ እንዲህ አሉ "አላህ የሁዶችን ረገመ። አላህ ሞራን ከመጠቀም የከለከላቸው ጊዜ አሳምረው ሸጡትና የሸጡበትን ዋጋ በሉት።" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ጃቢር ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መካ በተከፈተበት ዓመት መካ ሳሉ እንዲህ ሲሉ ሰማቸው "አላህና መልክተኛው አስካሪ መጠጥን፣ በክትን፣ አሳማንና ጣዖታትን ከመሸጥ ከልክለዋል።" ለርሳቸውም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! የበክት ሞራ መሸጥ ይፈቀድልናልን? ምክንያቱም በርሱ ጀልባዎቻችን ይጠገኑበታል፣ ቆዳዎቻችንን እንቀባለን፣ ሰዎች በርሱ ኩራዞቻቸውን ያበሩበታል።" ተባሉ። እርሳቸውም "በፍፁም እርሱን መሸጥም ክልክል ነው።" አሉና ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀጠል አድርገው እንዲህም አሉ: "አላህ አይሁዶችን ይርገማቸውና ያጥፋቸው አላህ በነርሱ ላይ የእንስሳ ሞራን የከለከለ ጊዜ አቅልጠው ቅባቱን ሸጡትና ዋጋውን በሉ።"

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/4556